<u>ታህሳስ 10/2012 ዓ.ም</u>

# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ዛሬ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአንዳንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ወቅታዊ ሁኔታ ምክንያት በማድረግ ካሉት ሰባት ግቢዎች በሶስቱ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ያለመከታተል ችግር በአራቱ ግቢዎች ግን መማር ማስተማሩ በተለመደው ሁኔታ መቀጠሉን በመገንዘብ የዩኒቨርሲቲው አመራር፣ መምህራንንና ተማሪዎች የሚወከሉበት ከፍተኛው የውሳኔ ሰጪ አካል (ሴኔት) በጉዳዩ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፉ ይታወሳል።

በውሳኔው መሰረትም ተማሪዎቹ <u>እስከሰኞ ታህሳስ 6 ቀን 2012 ዓ.ም</u> ድረስ በተለመደው አኳኋን ትምህርት እንዲቀጥሉ፤ ይህ ሳይሆን ቢቀር ተማሪዎቹ <u>በራሳቸው ፈቃድ ትምህርት ለማቋረጥ እንደወሰኑ</u> ተቆጥሮ ዩኒቨርሲቲው ይህን ውሳኔ ተፈጻሚ እንደሚያደርግ አሳውቆ ነበር። በዚህ ውሳኔ መሰረትም ትምህርት አቋርጠው የነበሩ የሁለት ግቢዎች ተማሪዎች ወደትምህርት ሲመለሱው የባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት (BiT) ተማሪዎች ይህንን ሴኔቱ የሰጠውን እድል ሳይጠቀሙበት በመቅረታቸው ግቢውን በራሳቸው ጊዜ ለቀው ወጥተዋል።

ዩኒቨርሲቲው ወደዚህ ውሳኔ ከመምጣቱ በፊት፡

1ኛ. በተፈጠሩ አለመረጋጋቶች ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የተፈናቀሉ ተማሪዎችን የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በዩኒቨርሲቲዎቹ ሰላማዊ ሁኔታ እንዲፈጠር በማድረግ ተማሪዎቹ ወደነበሩባቸው ተቋማት ተመልሰው በሰላም ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ በሚቻልበት መንገድ ላይ የመፍትሄ አካል መሆን እንጂ ትምህርት ማቋረጥ ለችግሩ መፍትሄ እንደማይሆን ለረዥም ጊዜ ለተማሪዎቹ ሲያሳስብ ቆይቷል፤

2ኛ. ተማሪዎቹ መደበኛ የመማሪያ ጊዜያቸው እየተስተጓጎለ በመሆኑ "አልተረጋጋንም ጊዜም ያጥረናል" የሚል ጥያቄ በማንሳታቸው የወሰነ ትምህርት አጋማሽ ፈተና መስጫ ጊዜው እንዲራዘምላቸው ተደርጓል፤ ይሁንና የተራዘመው የአጋማሽ ፈተናም በተቀመጠለት ጊዜ ሳይጀመር በመቅረቱ የባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሴኔት በ26/03/2012 ዓ.ም ባካሄደው አስቸኳይ ስብሰባ፡

ሀ) እንዲካሄድ የታቀደው አጋማሽ ፈተና ለጊዜው እንዲቋረጥና ተማሪዎች ወደክፍል ገብተው ትምህርታቸውን እንዲማሩ፤

ለ) የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲቋረጥ መሪ ተዋናይ ሆነው የተገኙት ስምንት ተማሪዎች ከዚህ በፊትም ከፈተና ጋር በተያያዘ ትምህርት አንማርም ብለው በመወሰናቸው የዲሲፕሊን ርምጃ እንዲወሰድባቸው ተወስኖ ወቅታዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ውሳኔው ተፈጻሚ ሳይደረግባቸው ከቀሩ የአንድ ባች ተማሪዎች ውስጥ የነበሩ በመሆናቸው፤

ነገር ግን አሁንም በድጋሜ የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲቋረጥ የመሪነት ሚና እየተጫዎቱ ለመሆኑ ማስረጃ የቀረበባቸው በመሆናቸው የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ባደረገው የተማሪዎች

Federal Democratic Republic of Ethiopia Bahir Dar University

የዲሲፕሊን መመሪያ መሰረት የኢንስቲትዩቱ አመራር፣ መምህራንንና ተማሪዎች የተወከሉበት ሴኔት ሁለት ተማሪዎች ላይ ለሁለት እና ስድስት ተማሪዎች ላይ ደግሞ ለአንድ ዓመት ከትምህርት ገበታቸው እንዲታገዱ በመወሰን ለተማሪዎቹ ውሳኔው እንዲደርሳቸው አድርጓል፤

3ኛ. ተማሪዎቹ የዲሲፕሊን መመሪያው በሚያዘው መሰረት የተቀጡ ሆነው ሳለ ቀሪው የኢንስቲትዩቱ ተማሪዎችና የሌሎች ሁለት ግቢዎች ተማሪዎች እነዚህ ተማሪዎች ወደትምህርት ካልተመለሱ ትምህርት አንማርም በማለታቸው ይህ ውሳኔያቸው ጠቃሚ እንደማይሆን ይልቁንም የተቀጡት ተማሪዎች በህጋዊ መንገድ ይግባኝ የሚሉበትና ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ የተቀጡ መሆኑ ከተረጋገጠ የሚመለሱበት ህጋዊ አካሄድ ሊኖር እንደሚችል አምነው እነርሱ ግን ትምህርት በመቀጠል በዩኒቨርሰቲው ለሚደረገው ሰላማዊ መማር ማስተማርን የማስፈን ጥረት የበኩላቸውን መወጣት እንደሚጠበቅባቸው በተለያዩ አካላት ውይይቶች ቢደረጉም አቋማቸውን መቀየር አልቻሉም።

ይህ ሁሉ ሲሆን ተማሪዎች በግቢ ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ እያገኙ ነገር ግን ትምህርት ለመማር ፈቃደኛ ሳይሆኑ ከአንድ ወር በላይ ቆይተዋል። ከዚህ በኋላ ዋናው የዩኒቨርሰቲው ሴኔት ተሰብስቦ ተማሪዎቹ ትምህርት እንዲጀምሩ (ከታህሳስ 2 እስከ 6 ቀን 2012 ዓ.ም) የመጨረሻ እድል ሰጥቶ ይህ ባይሆን በራሳቸው ፈቃድ ከዩኒቨርሲቲው ለመሰናበት እንደወሰኑ እንደሚቆጠር ካሳሰበ በሁዋላ ሌሎች ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ትምህርት ሲጀምሩ አሁንም የኢንስቲትዩቱ ተማሪዎች የሴኔቱን ውሳኔ ባለመቀበል ከግቢያቸው ወጥተወል።

ዩኒቨርሲቲውና ሌሎች አጋር አካላት (የባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር፣ የጸጥታ አካላት የአገር ሽማግሌዎችና የባሕር ዳር ከተማ ወጣቶች) በሚያስመሰግን ደረጃ ተማሪዎቹ ሰላማዊ መማር ማስተማር ሁኔታ ውስጥ እንዲገቡ ለማስቻል በተደጋጋሚ ሲያደርጓቸው የቆዩዋቸውን ጥረቶች ባለመረዳት ወይም ደግሞ በመካድ ተማሪዎቹ ያለበቂ ምክንያት ከግቢ ውጡ እንደተባሉ በማስመሰል በማህበራዊ ሚዲያ የሚራገቡ መረጃዎች የተሳሳቱ እንደሆኑ ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች ወላጆችም ሆነ በተቋሙ ሰላማዊ መማር ማስተማር ሰፍኖ ማየት ለሚወዱ አካላት ማሳዎቅ ይወዳል።

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንደመሆኑ መጠን ሁሉም ተማሪዎች በእውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ታንጸውና የሀገርና ወገናቸውን ችግሮች የሚፈቱባቸውን አቅሞች አጎልብተው እንዲወጡ ለማድረግ የሚተጋ ተቋም በመሆኑ ይህንን ለማረጋገጥ የሚያስችለውን ሰላም ለማምጣት ሁሉም ባለድርሻ አካላት (ተማሪዎች፣ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች፣ የተማሪዎች ወላጆች፣ በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት) ኃላፊነት መሆኑን ያምናል።

በዚህ አጋጣሚ እነዚህን ሁኔታዎች ወደተለመደው ሁኔታ በመመለስ በዩኒቨርሲቲያችን ሰላማዊ መማር ማስተማር እንዲቀጥል ለማድረግ ለቀናት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ከዩኒቨርሲቲው ጋር ተቀናጅተው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ለቆዩ አጋር አካላት (ለባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር፣ ለጸጥታ አካላት፣ ለአገር ሽማግሌዎችና ለባሕር ዳር ከተማ ወጣቶች) ዩኒቨርሲቲው ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል።

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ